# መብት ሀይማኖት፤ ፖለቲካ ሀይማኖት

በሰሞኑ የወያኔ የፀጥታ መስሪያ ቤት የአደናጋሪ ፕሮፓጋንዳ ክፍል ያቀነባበረው ፀያፍ ቪዲዮ በድረ ገፆች በመሰራጨት ላይ ነው። እስላሞች ፀረ ክርስቲያን ናቸው፤ ሀገሪቷን ሊቆጣጠሩ እያሴሩ ናቸው የሚል መልዕክትን ያዘለ ቪዲዮ ነው ወያኔ ያሰራጨው በሽፋን። የሀይማኖት ጉዳይ በሀገራችን አሳሳቢ ቦታን እያየዘ መሆኑ ግልፅ ነውና መብት፤ ሀይማኖትና ፖለቲካ ያላቸውን ዝምድናና ትስስር መተንተኑና መገንዘቡ አስፈላጊ ነው። በሁሉም መስክ ፅንፈኝነ ት ከሰፈነ ሀገራችን ወደ አስከፊ መቀመቅ መውረዷ አይቀሬ ይሆናል። ኢትዮጵያ ያለችበት ንም ቦታና የአካባቢዋን ሁኔታም ማጤኑ የዚህን ችግር አንደምታ ጠቋሚ ነው፡

በቅድሚያ የመብትን ይዘት በተመለከተ ምንም የተዛባ ግንዛቤ ሊኖር አይገባም። መብት ሙሉ እንጂ የተሸራረፈ አይደለም/ሊሆንም አይችልም። አንድ ሀገር የሰፊውን ሕዝብ መብት አክብሯል አስከብሯል ሊባል የሚቻለው የሕግ የበላይነት ሰፍኖ ቢያንስ ብዙሃኑ ባለ መብት ሆነው ሲገኙ ነው። መብት ሲባልም በወረቀት ወይም ሕዝብ መንግስት በሚባለው ላይ መስ ፈሩሳይሆን ተግባሪዊ ሆኖ መገኘቱ ነው ዋናው ቁም ነገር። የአፄ ኃይለስላሴ ህገ መንግሥት ብዙ መብቶችን ያረገግጥ ነበር--በተግባር ግን መብትም እኩልነትም አልነበረም። ይህም ሁኔታ  በአገዛዙ ላይ አብዮትን አመጣበት። የሀይማኖች እኩልነትና መብት አለመኖሩን በመቃወም እስላም ኢትዮጵያውያን ሲሰለፉ በክርስቲያን ዜጎች መታጀባቸው የማይረሳ የታሪክ ቅርስ ሆኗል። መብት ለወንድ ተሰጥቶ ለሴቶች ከተከለከለ መብት አለ ሊባል አይቻልም። መብት ለጥቂቶች ተሰጥቶ ለሌሎች ከተከለከለ ሀገሪቷ መብት አልባ ነች። ስለዚህም በማንኛውም ማጠየቂያና ሰበብ መብት ከተሸራረፈ መብት አልሰፈነም፤ ጭቆና አለ መባሉ ትክክል ነው ። ስለዚህም ሀይማኖትን ማጠየቂያ በማድረግ መብትን ለመገደብ የሚወሰድ እርምጃ ሁሉ ፀረ ዴሞክራሲያዊ ነው። በብሔረሰብ፤ በፆታ፤ ወዘተ ልዩነት ከተደረ ገና መብትም ከተነፈገ ይህ ሁኔታ ለትግልና ለአመፅ መገፋፋቱ የሚጠበቅና ፍትሀዊም ነው። ደርግ ስልጣን ሲይዝ ዴሞክራሲ አለገደብ፤ መብት ሳይሸራረፍ ይረጋገጥ ብሎ ሕዝብ ከኢሕ አፓ ጋር በመሆን ያካሄደው ትግልና የከፈለው መስዋዕትነት ሊረሳ አይገባውም። መብት ሲነሳ የሀገሪቷም ተጨባጭ ሁኔታ በዚያው መነሳት መመርመር ይገባዋል። ይህ ቢባልም ግን ሁኔታዎች ከሀገር ሀገር ይለያያሉና ለአሜሪካ ሕዝብ ያስፈልገዋል የሚባለው መብት ለአፈሪ ካውያን ይበዛባቸዋል የሚለው ድምዳሜ ከቶም ትክክል አይደለም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ደር ግን ሲታገል ቀበጠ ያሉትን አንረሳቸውም። የዴሞክራሲ መብት ለአሜሪካና ለነጮች ይሁን ያህል ግን ለጥቁሮች ደግሞ ቀነስ ተደርጎ እንደዚህ የሚሉ ዘረኞች ብቻ ናቸው። በኢትዮጵያ ጋዜጠኞች መታሰራቸውን ስንቃወም በኤርትራም ሆነ በባሕሬይንም ይህ ሲደረግ መቃወም አለብን። ትምህርት ቤት የሚሄዱ ሴት ሕፃናት ላይ አሲድ በፊታቸው ሲወረወር መቃወምና

ማወገዝ እንዳለብን ሁሉ በሀገራችንም ላቅመ ሔዋን ያልደረሱ ሴቶች ለግድ ጋብቻ  ሲሰጡ ወይም ለባዕድ ሲሸጡ እሪ እምቢ ማለት ይጠበቅብናል፡፡ የሕዝብ መብት በቅንጣትም ቢሆን ሲነካ መቃወም የሚጠበቅ ነው፡፡

መብትና ሀይማኖት ስንልም በመሰረቱ ሁለም በእምነቱ የመሰማራት መብት እንዳለው ማመን አስፈላጊ ነው፡፡ በሀይማኖት የተነሳ የሚደረግ ልዩነትና ጭቆና በሞላ አለምንም ማወላወል ተወጋዠና ፀረ ዴሞክራሲያዊ ነው፡፡ ማንኛውም ዜጋ የራሱን እምነት የመያዝ መብት እንዳለው መታወቅና መከበር አለበት፡፡እስላም ክርስቲያን ከሚሉትም ባሻገር የተለየ እምነት ያላቸው ዜጎችና ሕዝቦችም አሉ፡፡ ሀይማኖታዊ እምነት የሌላቸውም እንዳሉ ማወቅ ተገቢ ነው፡፡ ለዚህም ነው የማመንም ሆነ ያለማመን መብት ይከበር መባሉን መረዳት የሚኖ ርብን፡፡ በግብፅ 10 በመቶው ሕዝብ የኮፕት ክርስቲያን ነው- መብቱ ተደፍሮና ተረግጦ ቤተክርስቲያኑ ማቃጠልና አማኙም መጠቃት የለበትም፡፡ መስጊድ ማቃጠል ሆነ  ክርስቲያ ኑን ማረድ ከዴሞክራሲና መብት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፡፡ የተወሰኑ ፅንፈኞች በሚያ ደርጉት የተነሳ መላ አማኞች በጅምላ በአሉታዊ ተፈርጀው በዚሁም ሕዝብና አማኝ በአጠ ቃላይ ሽብርተኛ የሚባልበትን ሁኔታ ማስተናገድ አይገባም፡፡ ዛሬ በሁሉም የሀይማኖት መስ ክ ጭፍን አክራሪዎች ፈልተዋል፡፡ ለሌሎች እምነቶች ትዕግስትም የላቸውም፡፡ ቀደም ያልተ ሰማና ያልታወቀ ጥላቻና አለመቻቻልን ያራግባሉ፡፡ አዎ ዘመን ተለውጧል--አክራሪዎች ገነዋል፡፡ ይህ ግን ተቀባይነትን ሊያገኝ የሚችል መሆን የለበትም፡፡ ፅንፈኛዎችን ሁሉ አለም ንም ለቀቅተኝነት መታገል አለብን፡፡ በሀይማኖት ሽፋን በሕዝብ ላይ ጥቃት የሚያደርሱና ወንጀል የሚፈፅሙ ሕዝባዊ ቁጣና ቅጣትን እንደሚቀበሉ ማወቅ አለባቸው፡፡

ሳላፊስት አልቃይዳ፤ ፐንቴኮስቴ ጄሆቫህ፤ ኦርቶዶክስ ካቶሊክ  ሁሉም ከእምነቱ ባሻገር በሀገ ር ፖለቲካ ገብቶ ጥላቻንና መፈራረቅን አንግሶ ከተሰማራ ከሀገር ደህንነትና አንድነት አንፃር ሚናው አሉታዊ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ሀይማኖትና መብት ስንል እምነት የግል ሀገር የጋራ የሚለውን መሰረት አድርገን ነው፡፡ ኢትዮጵያ የክርስቲያን ሀገር ናት ብሎ ብዙ ሕዝብን መካድ፤ ኢትዮጵያን የእስላም ሀገር አድርገን እንገዛለን ብሎ በወያኔው ቪዲዮ እንደታየው ማጓራት፤ የሌላውን ሀይማኖት ማንኳሰስ፤ እርስ በርስ ቅራኔን ማፈፋም በቸልታ የሚታለፍ ሊሆን አይችልም፡፡  ዴሞክራሲ ከተባለ ሀይማኖትና ፖለቲካ መለያየታቸው ዋና ጉዳይ ነው፡ ፡ ሁለቱ ሲደባለቁ ነገሮች ሁሉ ይተራመሳሉ-- በሕዝብ መሀልም ልዩነት ይሰፍናል፡፡ አንድ ሀይማኖት ያላቸውም ሕዝቦች--ለምሳሌ ሶማሌዎች ሲፋጁ--እያየን ነው፡፡ በኢራቅም ሆነ ሌሎች ሀገሮች በዋና ሀይማኖት ልዩነት ሳይሆን ሱኒ ሺያ በሚል  ጦርነት አለ ፡፡ በአየርላን ድ ካቶሊኮችና ፕሮቴስታንቶች ተፋጅተዋል ፡፡ ለዚህም ነው የሀይማኖት ጉዳይ በጥንቃቄ መያዝ አለበት የሚባለው፡፡ ጥንት የክሩሴድ ጦርነት የተባለው በኢየሩሳሌም ለስንት ዓመታ

ት መካሄዱን ማስታወስ ተገቢ ነው። ለዚህም ነው ሀይማኖት የግል ይሁን ሀገር ግን የጋራ መሆን አለበት የሚለው መርሕ ለሀገር ግንባታ ጠቃሚ ነው ተብሎ የሚወሰደው።

ይህም በመንግሥት ስርዓት ደረጃ ሲገለጥ ሀይማኖትና ፖለቲካ መለያየት አለባቸው የሚለውን መሰረታዊና ዴሞክራሲያው መርህ በግንባር ያቀርበዋል። ሀይማኖት በፖለቲካ ጣልቃ አይግባ ሲባል አንዳንዶች ይህ ኮሙኒዝም ነው ወይም ሀይማኖትን መካድ ነው ብለው ይደመድማሉ-- ይህ ግን አለማወቅ ነው። ሀይማኖትና ፖለቲካ ይለዩ ወይም ፈረንጆች እንደሚሉት ሴኩላሪዝም የተባለው ስርዓት ይስፈን የሚባለው በሀይማኖት መሀል ልዩነት ሆነ ግጭት እንዳይፈጠር ለማድረግ ነው። አንድ ሀይማኖት ባለበትም ሀገር ይህን እምነት መሰረት አድርጎ የሚወሰድ አቅዋምና እርምጃ ህገወጥ መሆኑ ግልፅ ነው። በምዕራብ ሀገሮች የሚታየው ፀረ እስላም አቅዋም ምሳሌ ነው። በአንዳንድ አረብና ሙስሊም ሀገሮች ደግሞ ሻሪያ በሚል ሽፋን  እየተካሄደ ያለው የሰብዓዊ መብት ረገጣ በዝምታ የሚታለፍ አይደለም። አንድ ሀይማኖት ባለበት ሀገር የሚወሰዱ እርምጃዎችን መረዳት ቢቻልም ( የምንደግፈው ባይሆንም) ልዩ ልዩ ሀይማኖቶች ባሉበት ሀገር ደግሞ በአንድ ሀይማኖት መሰረት ሀገርን እንግዛ ማለቱ በጣም ጎጂ መሆኑ አከራካሪ አይደለም። በቅርቡ ታየ በተባለው ፀያፍ ቪዲዮ የተደነፋው ኢትዮጵያን የእስላም ሀገር እናደርጋታለን ሆነ ሀገሪቷ የክርስቲያን ደሴት ናት የሚል አግላይ አቅዋም ከተጨባጩ ሁኔታ ጋር የተዛመደ ሳይሆን ሀገርን ለጥፋት ሊዳርግ የተነሳ አቀዋም መሆኑን መገንዘብ እንችላለን። ዴሞክራሲያዊ ኢትዮጵያን እንፈልጋለን ካልን ዘንዳ ይህች ኢትዮጵያ ልትከሰትና ልትገነባ የምትችለው በዴሞክራሲ መብቶች አለምንም ገደብና መሸራረፍ መከበር፤ በሕዝብና በሀይማኖቶች እኩልነትና በሀገራዊ አንድነት መሆኑ መታወቅ አለበት። ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ፖለቲካ ሀይማኖትን ለይታ የሕዝብን ሙሉ መብት አክብራ መገኘት መቻል ያለባት ናት። እስላም ክርስቲያን በሚል የግጭትና የጥላቻ አዙሪት ገብቶ መናከስ ከሰፈነ ግን ሀገር ለማንም ሳተሆን ለጥፋት መዳረጓ የማይቀር ነው። የሕዝብን መብት የሚፃረር የሀይማኖት ፅንፍ ደግሞ ፀረ ዴሞክራሲ ነው። የአፍሪካ ሀገሮችን ሊበታትኑ ለሚፈልጉ ምዕራባውያን አመቺ መሳሪያ ነው። ዛሬ በሀይማኖትና በብሄረሰብ መሰረት ፀረ ኢትዮጵያ ዘመቻ የያዙትን ባዕዳን ማየቱ በቂ ነው።

የዜጎች የግል እምነት ጉዳይ ሁሌም ስሜትና ቀስቃሽ ጉዳይ ነው። ዜጎች በእምነታቸው ፅኑ ናቸው። ለማተባቸው እንበልና ወይም ለእምነታቸው ሟች ናቸው። ለዚህም ነው የሁሉንም እምነት ማክበር የሚገባው። ሀይል አለን በሚል የተለየ አምነት ያለውን ለመጥቃት ለመፍጀት መነሳት ምን ጊዜም የሚያዋጣ አይደለም። ወያኔ ዛሬ ሱዳን በየቦታው ቆንስላ ይክፈት ብሎ ሲፈቅድ አለምክንያት አይደለም። ወያኔ አንዳንድ የባዕድ ሰባኪዎችን ኑ ስበኩ ብሎ ሲጠራ እንዲሁ አይደለም። ወያኔ ካድሬውን ጳጳስ ብሎና የራሱን ካድሬዎች በሙስሊሞች

ላይ ጭኖ የፈለገውን ሲያስፈፅም አለግብ አይደለም። ስልትና ዕቅድ አለ በወያኔው ተንኮል። ግቡ ሕዝብን መከፋፈል ነው። ዜጎች በሀይማኖት ከተናከሱ ደስታው ነው። ይህን ለማረጋገጥ በግልፅም በስውርም ይጥራል። ቤተክርስቲያን ያቃጥላል፤ እስላሞችንም ያጠቃል። ቅጥረኛ ሆዳሞቹንም በዚሁ ያሰማራል። በብሄረሰብም ደረጃ ያናክሳል። ፀረ ኢትዮጵያ ባዕዳንም በዚሁ ጥልቅ ይላሉ። በገንዘብና በተንኮል ሕዝብን በመከፋፋል በማጋጨት ተሰማርተው ለወያኔ ድጋፍ ይሰጣሉ። ይህን ሁሉ ነቅቶ ማወቅና ለማከሸፍም መታገል የዜጎች ሁሉ ግዴታ ነው። የሁሉም ዜጋ ሀገርን ዴሞክራሲያዊ አድርጎ እውን ለማድረግ መሰረቱ የሕዝብ አንድነ ት ነው። የሕዝብ አንድነት እውን ይሆን ዘንድ ደግሞ ፖለቲካና ሀይማኖትን ለይቶ መያዝ መሰረታዊ ነው። የአንዱን እምነት በሌላው ላይ በሀይል ለመጫን መነሳት ከቶም አያዋጣም ና ። መቻቻልና ሀይማኖት የግል ሀገር የጋራ የሚለውን መርህ መቀበል መሰረታዊና አማራ ጭ የሌለው ነው።

ከዚህ ተያይዞ ክብደትና ሚዛን ተሰጥቶት መቅረብ ያለበት ሌላ አቢይ ጉዳይ የሰብዓዊ መብት ተከራካሪና አስከባሪ ተቋሞች መኖራቸው ነው። ይህን ግብ ይዘው የተነሱ ተቋሞች ካሉን በመሰረቱ ለመብት ደረጃ በልዩነትና ከለልተኛነት የሚንቀሳቀሱ አይሆኑምና፤ መሆን የለባቸወምና ለሁሉም ዜጋ መብት አለልዩነት የሚታገሉልን ስለሚሆኑ ሀቀኛ የሰብዓዊ መብት ኮሚቴዎችና ተቋሞች መኖራቸው በጣም አስፈላጊ ነው። ለዚህም ነው ሀቀኛ የሰብዓ ዊ መብት ኮሚቴዎችን መደገፍና ማጠናከር የሚገባው---የሁላችንንም መሰረታዊ መብት ለማስከበር የሚታገሉ ናቸውና። መንግስት የተባለው በዚህ በዚያ ምክንያት የሕዝብን መብት ሲጥስ የሰብዓዊ መብት ኮሚቴዎች ይህን በመፃረር የሕዝብ ድምፅ ሆነው አስፈላጊና ጠቃሚ ሚናቸውን ያሟላሉ። ለዚህም ነው የሰብዓዊ መብት ኮሚቴዎችና መኖራቸውና መጠናከራቸው ወሳኝ ጉዳይ የሚሆነው። የሰብዓዊ መብት ኮሚቴ ስንልም ለሁሉም ዜጋ ፤ ለተጠቃው ሁሉ የሚቆሙና የሚሟገቱትን ማለታቸን ነው እንጂ " የእኛ እስረኞች ጉዳይ ብቻ" የሚሉ ከለልተኞችን አይመለከትም። እስላም ክርስቲያን፤ አማራ ኦሮሞ ወዘተ በሚል ልዩነት የማይፈጥሩ የሰብዓዊ መብት ተሚጋች ድርጅቶችን መደገፍና ማጠናከር ይገባል።

መብት ሙሉና የማይገደብ የማይሸራረፍ ነው። ፓለቲካና ሀይማኖትም መለያየታቸው ወሳኝ ነው። ሀገር የጋራ ናት--ሀይማኖት ግን የግል ነው። ተቻችለን ተግባብተን በሰላምና በዴሞክራሲ መኖር መቻል አለብን። በብሄረሰብ ሆነ በሀይማኖት መቃቃርና መካረር ሀገርን ይጎዳል፤ሊያጠፋም ይችላል። ለዚህም ነው ጥንቃቄ የሚያስፈልገው። ለወያኔ ሰለባ እንዳንሆ ን ። ኢትዮጵያን ሊያጠፉ ለሚሹ ባዕዳን ሁሉ መሳሪያ እንዳንሆን። ሀገራችን በዴሞክራሲ

እንድትገነባ ከፈለግን የመብትን ሙሉነት መቀበልና በዚህም በዚያም ሰበብ የሕዝብ መሰረታዊ መብት እንዳይገደብ መታገል አለብን፡፡ በኢትዮጵያ የአንድ ህይማኖት ወይም የአንድ በብሄረሰብ የበላይነት ሊሰፍን መፍቀድ አንችልም፡፡ ሊሆንም አይችልም/አይገባም፡፡ ስሊዚህም ነው ለወያኔ አውቀንም ሆነን ሳናውቅ ሰለባ እንዳንሆን እንጠንቀቅ! የሕዝብ አንድነት ለሀገር ህልውና መሰረት ነው፡፡ የሕዝብን አንድነት ማናጋትና ማጥቃት ደግሞ ሐጢያትም ወንጀልም ነው፡፡